# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

ታኅሣስ ፲ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም

## <u>የኅብረቱን የተግባር ኮሚቴ አባል የአቶ ተስፋየ ሐጎስን ድንገት መጥፋት  በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የፖለቲካ ጉዳይ ኮሚቴ አባል አቶ ተስፋየ ሐጎስ ከኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ጀምሮ የት እንደደረሱ ማወቅ አልተቻለም፡፡
አቶ ተስፋየ ሐጎስ በኅብረቱ የፖለቲካ ጉድዮች ኮሚቴ ጉልህ ሚና ያላቸው ሲሆን ኅብረቱ ለሕዝብ ድምፅ መከበር፥ ለፍትኅ፥ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር እያካሄደ ላለው ሰላማዊ ትግል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ምክንያት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ተደጋጋሚ ማስፈራራትና ዛቻ ሲደርስባቸውና የማሳደድ ዘመቻ ሲካሄድባቸው እንደነበር በኅብረቱ አመራርና አብረዋቸው በቅርብ በሚሰሩ ታጋይ ባልደረቦቻቸው ዘንድ ስለሚታወቅ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩና ሁልጊዜም ስለ ደኅንነታቸው ኅብረቱ ስጋት እንደነበረው ታውቋል፡፡

የአቶ ተስፋየን መዳረሻ ለማወቅ ኅብረቱም፥ ለረጅም ጊዜ የታገሉበትና በፖለቲካ ጉዳይ ሃላፊነት የሚያገለግሉት ድርጅታቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና ቤተሰብ ከፍተኛ ያልተቋረጠ ጥረት ቢያደርጉም እስካሁን የት እንዳሉና ምን እንደደረሰባቸው ማወቅ ባለመቻሉ ስጋታችን ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጥቷል፡፡
ስለ አቶ ተስፋየ ሐጎስ ደኅንነት የኢሕአዴግ መንግሥት በቀጥታ ሃላፊነት እንዳለበት እየገለጽን መዳረሻቸውን በማሳወቁ በኩል አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

አፈና ይቁም!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር (Tel.No) 251-1530945 (Fax)

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645